፹ ወንጌል ዘማርቆስ ፩ ።

## ክፍል ፫፡ በእንተ እኂዞቱ ስብከተ ወኃርዮቱ ሐዋርያተ ።

፲፬ ወእምድኅረ አኀዝዎ ወሞቅሕዎ ለዮሐንስ መጽአ እግዚእ ኢየሱስ ገሊላ፡ ወሰበከ ወንጌለ መንግሥተ እግዚአብሔር ።

፲፭ ወይቤ በጽሐ ጊዜሁ ወቀርበት መንግሥተ ሰማያት ነስሑ ወእመኑ በወንጌል ።

፲፮ ወእንዘ የኃልፍ መንገለ ባሕረ ገሊላ ረከበሙ ለስምዖን ወለእንድርያስ እኁሁ እንዘ ያሤግሩ ውስተ ባሕር እስመ መሠግራነ ዓሣ እሙንቱ ።

፲፯ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ንዑ ትልውኒ ወእሬስየክሙ መሠግራነ ሰብእ ።

፲፰ ወኀደጉ መሣግሪሆሙ ወተለውዎ ሶቤሃ ።

፲፱ ወኃሊፎ እምህየ ሕቀ ረከበሙ ለያዕቆብ ወለዮሐንስ እኁሁ ደቂቀ ዘብዴዎስ ወለሊሁኒ ምስሌሆሙ ውስተ ሐመር ይሠርዑ ወያስተሣንዩ መሣግሪሆሙ ።

፳ ወጸውዖሙ በጊዜሃ ወኀደጉ ዘብዴዎስሃ አባሆሙ ምስለ ዐሳቡ ውስተ ሐመር ወሖሩ ወተለውዎ ።

## ክፍል ፬፡ በእንተ ምህሮቱ ውስተ ምኵራብ ወፈውሶቱ ዘጋኔን ።

፳፩ ወሖሩ ቅፍርናሆም ወቦአ በሰንበት ምኵራበ ወአኀዘ ይምህሮሙ ።

፳፪ ወአንከሩ ምህሮቶ እስመ ከመ መኰንን ይሜህሮሙ ወአከ ከመ ጸሐፍቶሙ ።

፳፫ ወሀሎ ፩ዱ ብእሲ ዘጋኔን ውስተ ምኵራብ ።

፳፬ ወአውየወ ወይቤ ምንት ብየ ምስሌከ ኢየሱስ ናዝራዊ መጻእከኑ ታጥፍአነ ነአምረከ ከመ አንተ ቅዱሱ ለእግዚአብሔር ።

፳፭ ወገሠፆ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ ተፈጸም ወፃእ እምኔሁ ።

፳፮ ወአስተራገፆ ውእቱ ጋኔን እኩይ ወአውየወ በዓቢይ ቃል ወወፅአ እምኔሁ ።

፳፯ ወደንገፁ ኵሎሙ እለ ርእዩ ዘንተ ወይቤሉ በበይናቲሆሙ ምንትኑ ዝንቱ ትምህርት ሐዲስ እስመ በትእዛዝ ይኤዝዞሙ ለአጋንንት ርኩሳን ወይትኤዘዙ ሎቱ ።

፳፰ ወተሰምዐ ነገሩ ውስተ ኵሉ በሐውርተ ገሊላ ።

## ክፍል ፭፡ በእኂተ ሐማተ ጴጥሮስ ።

፳፱ ወወፂአ እምኵራብ ቦአ ቤተ ስምዖን ወምስሌሁ እንድርያስ ወያዕቆብ ወዮሐንስ ።

፴ ወሐማቱ ለስምዖን ትፈዕን ወነገርዎ በእንቲአሃ ።

የማርቆስ ወንጌል ፩ ።

## ክፍል ፫፡ ትምህርት ስለ መጀመሩ ሐዋርያትን ስለ መምረጡ ።

ዮሐንስን ይዘው ካሰሩት በኋላም ጌታ ኢየሱስ ወደ ገሊላ መጥቶ የእግዚአብሔርን የመንግሥቱን ወንጌል ሰበከ። ማቴ ፬፡፲፪። ሉቃ ፬፡፲፬። ዮሐ ፬፡፵፫። ፲፬

ጊዜው ደረሰ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ገብታችሁ በወንጌል እመኑ አለ። ገላ ፬፡፬። ፲፭

በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲያልፍም ስምዖንና ወንድሙ እንድርያስን ዓሣ አሥጋሪዎች ነበሩና መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አገኛቸው። ማቴ ፬፡፲፫-፳፪። ሉቃ ፭፡፩-፲፩። ፲፮

ጌታ ኢየሱስም ኑ ተከተሉኝ ሰውንም የምታጠምዱ አደርጋችኋለሁ አላቸው። ፲፯

ያን ጊዜም መረባቸውን ትተው ተከተሉት። ፲፰

ከዚያም ጥቂት እልፍ ብሎ የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብንና ወንድሙ ዮሐንስን መረባቸውን ሲያበጃጁ አገኛቸው እሱም ከነርሱ ጋር በመርከብ ውስጥ ነበረ። ፲፱

ወዲያውም ጠራቸውና አባታቸው ዘብዴዎስን ከሙያተኞቹ ጋር በመርከቡ ውስጥ ትተው ተከትለዉት ሄዱ። ፳

## ክፍል ፬፡ በምኵራብ ስለ ማስተማሩና ጋኔን የያዘውን ስለ መፈወሱ ።

ወደ ቅፍርናሆም በሄዱም ጊዜ በሰንበት ከምኵራብ ገብቶ ያስተምራቸው ጀመረ። ሉቃ ፬፡፴፩-፴፯። ፳፩

ትምህርቱንም አደነቁ እንደ ጻፎቻቸው ያይደለ እንደ ጌትነቱ ያስተምራቸው ነበርና። ማቴ ፯፡፳፰-፳፱። ፳፪

በምኵራቡ ውስጥ ጋኔን ያደረበት አንድ ሰው ነበር። ፳፫

ናዝራዊው ኢየሱስ ሆይ! ካንተ ጋር ምን አለን ልታጠፋን መጣህን? አንተ የእግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆንክ እናውቃለን እያለ ጮኸ። ምዕ ፫፡፯። ፳፬

ጌታ ኢየሱስም ዝም በል ከእርሱም ውጣ ብሎ ገሠፀው። ምዕ ፭፡፰። ፳፭

ያ ክፉ ጋኔንም አንፈራፈረውና በታላቅ ቃል እየጮኸ ከእርሱ ወጣ። ምዕ ፱፡፳፮። ፳፮

ይህንንም ያዩ ሁሉ ደነገጡ፡ እርስ በርሳቸውም ይህ አዲስ ትምህርት ምንድነው? ርኩሳን አጋንንትን ውጡ ብሎ ያዛቸዋልና እነርሱም ይታዘዙታልና አሉ። ፳፯

ዜናውም በገሊላ አውራጃዎች ሁሉ ተሰማ። ፳፰

## ክፍል ፭፡ ስለ ጴጥሮስ አማት ።

ከምኵራቡም ወጥቶ ወደ ስምዖን ቤት ገባ፡ እንድርያስ፡ ያዕቆብና ዮሐንስ አብረዉት ነበሩ። ማቴ ፰፡፲፬-፲፯። ሉቃ ፬፡፴፰-፵፩። ፳፱

የስምዖን አማትም ሆድ ዝማ ታማ ነበርና የእሷን ነገር ነገሩት። ፴

## ወንጌል ዘማርቆስ ፬ ።

፬ ወእንዘ ይዘርእ ቦ ዘወድቀ ውስተ ፍኖት ወመጽኡ
አዕዋፍ ወበልዕዎ ።
፭ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ኰኵሕ ኀበ አልቦ መሬት
ብዙኀ ወፍጡነ በቈለ እስመ አልቦ ዕመቅ ለመሬቱ ።
፮ ወሠረቀ ፀሐይ አውዓዮ እስመ ኢኮነ እሙቀ
መሬቱ ወአልቦ ሥርው ወየብሰ ።
፯ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ሦክ ወሐነቆ ሦክ ወኢፈረየ ።

፰ ወቦ ዘወድቀ ውስተ ምድር ሠናይት ወበቈለ ወል
ሀቀ ወፈረየ ወወሀበ ፍሬ ቦ ዘሠላሳ፥ ወቦ ዘስሳ፥
ወቦ ዘምእት ።
፱ ወይቤሎሙ ዘቦ ዕዝን ሰሚዐ ለይስማዕ ።
፲ ወእምዝ በባሕቲሙ ተስእልዎ እሊአሁ ምስለ ዐሠ
ርቱ ወክልኤቱ አርዳኢሁ ምሳሌሁ ።
፲፩ ወይቤሎሙ ለክሙ ተውህበ ታእምሩ ምሥጢረ
ለመንግሥተ እግዚአብሔር ወለእለ አፍአሰ በምሳሌ
ይከውኖሙ ኵሉ ።
፲፪ ከመ ርእየ ይርአዩ ወኢያእምሩ፥ ወሰሚዐ ይስምዑ
ወኢይለብዉ ከመ ኢይነስሑ ወኢይትኀደግ ሎሙ ወኢ
ይትኃደግ ሎሙ ኃጢአቶሙ ።

፲፫ ወይቤሎሙ ኢተአምሩኑ ዘተ ምሳሌ እፎ እንከ ተእ
ምሩ ኵሎ አምሳለ ።

፲፬ ዘይዘርእሰ ቃለ እግዚአብሔር ይዘርእ ።
፲፭ ወእሉ እሙንቱ እለ ውስተ ፍኖት ኀበ ተዘርአ
ቃል ወእምከመ ሰምዑ ቃለ ይመጽእ ሰይጣን ሶቤሃ
ወይነሥእ እምልበሙ ቃለ ዘተዘርአ ።

፲፮ ወእሉ ካዕበ እሙንቱ እለ ውስተ ኰኵሕ እለ ይሰ
ምዑ ቃለ ዘተዘርአ ወይትዌከፍዎ ሶቤሃ በፍሥሓ ።
፲፯ ወአልበሙ ሥርው ለጊዜሃ ዳእሙ እሙንቱ ወእም
ከመሰ ኮነ ምንዳቤ ወስደት በእንተዝ ቃል የዐልዉ
ሶቤሃ ።
፲፰ ወእሉ እሙንቱ እለ ውስተ ሦክ ተዘርኡ እለ ይሰ
ምዕዎ ለቃል ዘተርዘአ ።
፲፱ ወሕሊና ዝንቱ ዓለም ወፍትወተ ብዕል ወበዕድኒ
ኵሉ ፍትወት ይበውእዎ ወየሐንቅዎ ለቃል ወኢ
ይፈሪ ።
፳ ወእሉ እሙንቱ እለ ውስተ ምድር ሠናይት ተዘ
ርኡ እለ ይሰምዑ ቃለ ወይትዌከፍዎ ወይፈርዩ
አሐዱ በሠላሳ፥ ወአሐዱ በስሳ፥ ወአሐዱ በምእት።
፳፩ ወይቤሎሙ ቦኑ የኀትዉ ማኅቶተ ከመ ያንብርዋ
ታሕተ ከፈር አው ታሕተ ዓራት አላ ከመ ያንብርዋ
ዲበ ተቅዋማ ።

## የማርቆስ ወንጌል ፬ ።

፬ ሲዘራም በመንገድ የወደቀ ወፎች መጥተው የበ
ሉት ዘር አለ ።
፭ ብዙ አፈር በሌለበት በድንጋይ ላይ የወደቀ ነገርን
ለአፈሩ ጥልቅነት የለውምና ፈጥኖ የበቀለ አለ ።
፮ ፀሐይም በወጣ ጊዜ አነደደው፥ አፈሩ ጥልቅ አልነ
በረምና ሥርም የለውምና ደረቀ ።
፯ በእሾኽም መካከል የወደቀ አለ፥ ነገር ግን እሾኽ
አንቆ ያዘውና አላፈራም ።
፰ በመልካም ምድር ላይ የወደቀ አለ፥ በቀለ፥ አደገ፥
አፈራ፥ ፍሬም ሰጠ፥ ሠላሳም ቅንጣት ያፈራ፥ ስድ
ሳም ቅንጣት ያፈራ፥ መቶም ቅንጣት ያፈራ አለ ።
፱ ዦሮ ያለው መስማትን ይስማ ።
፲ ብቻቸው በሆኑ ጊዜ አብረዉት የነበሩት ከዐሥራ
ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ምሳሌውን ጠየቁት ።
፲፩ ጌታ ኢየሱስም ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት
ምሥጢር ልታውቁ ተሰጥቷችኋል፥ በውጭ ላሉት
ግን ሁሉ በምሳሌ ይነግራቸዋል ። ፩ ቆሮ ፭፥ ፲፪ ።
፲፪ ማየትን አይተው እንዳያውቁ፥ መስማትንም ሰም
ተው እንዳያስተውሉ እንዳይመለሱ ይቅር እንዳ
ልላቸው ኃጢአታቸውም እንዳይሠረይላቸው ። ኢሳ
፮፥ ፱-፲ ። ማቴ ፲፫፥ ፲፬ ። ዮሐ ፲፪፥ ፵ ። ግብ ሐዋ
፳፰፥ ፳፮ ።
፲፫ እርሱ እንዲህ አላቸው፥ ይህችን ምሳሌ አታውቁ
ምን እንግዲያ ምሳሌዎችን ሁሉ እንዴት ታውቃ
ላችሁ ? ።
፲፬ የሚዘራ የእግዚአብሔርን ቃል ይዘራል ።
፲፭ ቃሉ በተዘራበት መንገድ የተመሰሉም እነዚህ
ናቸው፥ ቃሉ ከተዘራ ዘንድም ቃሉን እንደሰሙ
ያን ጊዜ ሰይጣን መጥቶ የተዘራውን ቃል ከል
ባቸው ይወስዳል ።
፲፮ ዳግመኛም በደንጊያ የተመሰሉ የተዘራውን ቃል
ሰምተው ፈጥነው በደስታ የሚቀበሉት ናቸው ።
፲፯ ነገር ግን ለጊዜው ተቀባዮች ናቸው እንጂ ሥር
የለባቸውምና ስለ ተማሩት ትምህርት መከራና ስደት
በመጣ ጊዜ ፈጥነው ይክዳሉ ።
፲፰ በእሾኽ ላይ በተዘራ ዘር የተመሰሉም የተዘራውን
ቃል የሚሰሙ እነዚህ ናቸው ።
፲፱ የዚህ ዓለም አሳብ ባለጠግነትን መውደድ ሌላውም
ምኞት ሁሉ ይገቡበትና ትምህርቱን ያንቁታል
እሱም አያፈራም ። ምዕ ፲፥ ፳፫ ። ፩ ጢሞ ፯፥ ፲፯ ።
፳ በመልካም ምድር የተዘሩት ቃልን ሰምተው የሚቀ
በሉት አንዱ ሠላሳ፥ አንዱ ስድሳ፥ አንዱ መቶ ቅን
ጣት የሚያፈሩ እነዚህ ናቸው ።
፳፩ መብራትን በመቅረዚ ላይ ሊያኖሯት ነው እንጂ
ዕንቅብ ሊደፉበት ወይም ከአልጋ በታች ሊያኖሯት
መብራትን በውኑ ያበሩሉን ? ማቴ ፭፥ ፲፭ ። ሉቃ
፰፥ ፲፮-፲፰ ።

አጋዘ እንዘ ይነብር ዳኅነ ወልቡ ገብአ ወልቡስ ልብሰ
ዝኩ ዘአኀዘ ሌጌዎን ወፈርሁ ።
፲፮ ወዜነውዎሙ እለ ርእዩ ዘከመ ኮነ ዘጋኔን ወዘበ
እንተ አሕርው ።
፲፯ ወአኀዙ ያስተብቍዕዎ ከመ ይፃእ እምደወሎሙ ።
፲፰ ወበሪጎ ሐመረ አስተብቍዖ ውእቱ ዘጋኔን ይሑር
ምስሌሁ ።
፲፱ ወከልኦ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ ሑር ቤተከ ኀበ
እሊአከ ወንግር ኵሎ ዘገብረ ለከ እግዚአብሔር
ወተሣሃለከ ።
፳ ወሖረ ወአኀዘ ይስብክ በዐሥሩ አህጉር ኵሎ ዘገ
ብረ ሎቱ እግዚእ ኢየሱስ ወአንከሩ ኵሎሙ ።
፳፩ ወከዐበ ዐደወ እግዚእ ኢየሱስ በሐመር ማዕዶተ
ወተጋብኡ ብዙኃ ሰብእ ኀቤሁ በኀበ ሐይቀ ባሕር ።

ክፍል ፳ወ፩፡ በእንተ ወለተ መጋቤ ምኵራብ።

፳፪ ወመጽአ ኀቤሁ አሐዱ ብእሲ መጋቤ ምኵራብ
ዘስሙ ኢያኢሮስ ወርእዮ ሰገደ ሎቱ ታሕተ እገሪሁ።

፳፫ ወብዙኀ አስተብቍዖ ወይቤ ወለትየ አልጸቀት
ትሙት ወበሕቱ ነዓ ደይ እዴከ ላዕሌሃ ወተሐዩ ።

፳፬ ወሖረ እግዚእ ኢየሱስ ምስሌሁ ወይተልውዎ ብዙ
ኃን ሰብእ ወይትጋፍዕዎ ።

ክፍል ፳ወ፪፡ በእንተ ብእሲት እንተ ይውኅዝ ደም።

፳፭ ወመጽአት ብእሲት እንተ ደም ይውኅዝ እምዐሠ
ርቱ ወክልኤቱ ክረምት ።
፳፮ ወብዙኀ አሕመምዋ ብዙኃን ዐቀብተ ሥራይ ወአ
ስተዋዕአት ኵሎ ንዋያ ወአኅለቀት ወአልበ ዘበ
ቍዓ ዘእንበለ ዳዕሙ ዘአልሐማ ፈድፋደ ።
፳፯ ወሰሚዓ በእንተ እግዚእ ኢየሱስ መጽአት ወበአት
ማእከለ ሰብእ ወገሠሠት ጽንፈ ልብሱ እንተ ድኅሬሁ።
፳፰ እንዘ ትብል እምከመ ገሠሥኩ ጽንፈ ልብሱ አሐዩ ።
፳፱ ወሶቤሃ ነጽፈ ነቅዐ ደማ ወአእመረት ርእሳ ከመ
ሐይወት እምደዌሃ ።
፴ ወአእመረ እግዚእ ኢየሱስ ሶቤሃ ከመ ወፅአ ኃይል
እምኔሁ ወተመይጠ ኀበ ሰብእ ይቤሎሙ መኑ ገሠ
ሠኒ ጽንፈ ልብስየ ።
፴፩ ወይቤልዎ አርዳኢሁ ትሬኢ ሰብአ እንዘ ይትጋፍ
ዐከ አንተሰ ትብል መኑ ገሠሠ ጽንፈ ልብስየ ።
፴፪ ወተመይጠ ከመ ይርአይ ዘገብረ ዘንተ ።
፴፫ ወፈርሃት ይእቲ ብእሲት ወርዕደት ጥቀ እስመ አእ
መረት ዘኮነ ላዕሌሃ ወመጽአት ኀበ እግዚእ ኢየ
ሱስ ወሰገደት ሎቱ ወነገረቶ ኵሎ ጽድቀ ።



በደኅና ተቀምጦ ያ ከፉ ሌጌዎን የያዘው ሰው አእ
ምሮው ተመልሶለት ልብሱን ለብሶ አገኙትና ፈሩ ።
ያዩ ሰዎችም ጋኔን የያዘው ሰው የሆነውንና በእሪያ ፲፮
ዎችም የተደረገውን ነገሯቸው ።
ከአገራቸውም ይወጣ ዘንድ ይማልዱት ጀመር ። ፲፯
ወደ መርከብ በወጣም ጊዜ ጋኔን ያደረበቱ ሰው ፲፰
ከእሱ ጋር ይሄድ ዘንድ ማለደው ።
ጌታ ኢየሱስም ከለከለው ወደ ቤትህ ወደ ወገኖ ፲፱
ችህ ሂደህ ይቅር ያለህ እግዚአብሔር ያደረገልህንም
ተናገር አለው ።
ሂዶም ጌታ ኢየሱስ ያደረገለትን ሁሉ በዐሥሩ አህ ፳
ጉር ይሰብክ ጀመር፡ ሁሉም አደነቁ። ምዕ ፯፡ ፴፩ ።
ዳግመኛም ጌታ ኢየሱስ በመርከብ ወደ ማዶ ተሻ ፳፩
ገረ፡ ብዙ ሰዎችም በባሕሩ ዳር ወደርሱ ተሰበሰቡ ።

ክፍል ፳፩፡ ስለ ምኵራቡ ሹም ልጅ ።

ስሙ ኢያኢሮስ የሚባል አንድ የምኵራብ ሹም ፳፪
የነበረ ሰው ወደ እርሱ መጣ በየውም ጊዜ ከእግሩ
በታች ወድቆ ሰገደለት ። ማቴ ፱፡ ፲፰-፳፮ ። ሉቃ
፲፡ ፵፩-፵፪ ።
ልጄ ልትሞት ደርሳለች፡ ነገር ግን እንድትድን ና ፳፫
እጅህን ጫንበት እያለ መላልሶ ማለደው ። ምዕ
፯፡ ፴፪ ።
ጌታ ኢየሱስም ከእርሱ ጋር ሄደ፡ ብዙ ሰዎችም ፳፬
ይከተሉትና ያጫንቁት ነበር ።

ክፍል ፳፪፡ ደም ይፈሳት ስለ ነበረችው ሴት ።

ከዐሥራ ሁለት ዓመት ጀምሮ ደም ይፈሳት የነበረች ፳፭
ሴት መጣች ።
ብዙዎች ባለ መድኃኒቶች እጅግ አባበሉባት ገንዘ ፳፮
ቧን ሁሉ ሰጥታ ጨረሰች ግን እጅግ እያደከማት
ከመሄዱ በቀር የረባት የጠቀማት የለም ።
የጌታ ኢየሱስን ዝና በሰማች ጊዜ መጣችና በሰው ፳፯
ማኸል ገብታ በስተኋላው የልብሱን ጫፍ ዳሠሠች ።
የልብሱን ጫፍ የዳሠሥኩ እንደሆነ እድናለሁ ብላ ። ፳፰
ያን ጊዜም የደሟ ምንጭ ደረቀ፡ ከደዌዋ እንደ ፳፱
ዳነች ራሷ አወቀች ። ዘሌ ፳፡ ፲፫ ።
ጌታ ኢየሱስም ኃይል ከእሱ እንደ ወጣ አውቆ ወደ ፴
ሰዎች መለስ ብሎ የልብሴን ጫፍ ማን ዳሠሠ?
አላቸው ። ሉቃ ፯፡ ፲፱ ።
ደቀ መዛሙርቱም ሰው ሲያጋፋህ ታያለህ፡ አንተ ፴፩
ግን የልብሴን ጫፍ ማን ዳሠሠኝ ትላለህ? አሉት ።
ይህንም ያደረገውን ሊያይ መለስ አለ ። ፴፪
ያች ሴት ግን ፈርታ እጅግ ተንቀጠቀጠች በርሷ ፴፫
ላይ የሆነውን ተአምራት አውቃለችና፡ ወደ ጌታ
ኢየሱስም መጥታ ሰገደችለት እውነቱንም ሁሉ
ነገረችው ።

## ወንጌል ዘማርቆስ ፭ ።

፴፬ ወይቤላ ወለትየ ሃይማኖትኪ አሕይወተኪ እትዊ
በሰላም ወሕየዊ እምደዌኪ ።
፴፭ ወእንዘ ይትናገር ምስሌሃ መጽኡ ሰብአ ኀበ መጋቤ
ምኵራብ ወይቤልዎ ወለትከሰ ሞተት ወኢታሻ
ምዎ እንከ ለሊቀ ።
፴፮ ወሰሚዖ እግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይትናገርዎ ይቤሎ
ለመጋቤ ምኵራብ ኢትፍራህ ተአመን ዳእሙ ።
፴፯ ወኢኀደገ ከመ አልቦ ዘይተልዎ ዘእንበለ ጴጥሮስ
ወያዕቆብ ወዮሐንስ እኁሁ ለያዕቆብ ።
፴፰ ወቦአ ቤቶ ለመጋቤ ምኵራብ ወረከቦሙ እንዘ ይት
ሀወኩ ወይበክዩ ወየአወይዉ ብዙኀ ።
፴፱ ወቦአ ወይቤሎሙ ለምንት ትትሀወኩ ወትበክዩ
ሕፃንሰ ኢሞተት አላ ትነውም ወሰሐቅዎ ።
፵ ወአምኀዘ ሰደደ ኵሎ ወነሥአሙ ለአቡሃ ወለእማ
ለሕፃን ወእለ ምስሌሁ ወቦአ ኀበ ሀለወት ሕፃን ።
፵፩ ወአኀዘ እዴሃ ለሕፃን ወይቤላ ፡ ጣቢታ ቁሚ ተን
ሥኢ ወለትየ ብሂል በትርጓሜሁ ።
፵፪ ወተንሥአት ሶቤሃ ይእቲ ወለት ወአንሶሰወት ወዐ
ሠርቱ ወክልኤቱ ክረምታ ፡ ወደንገፁ ሶቤሃ ዐቢየ
ድንጋፄ ።
፵፫ ወገሠፆሙ ለአቡሃ ወለእማ ብዙኀ ከመ አልቦ ዘየ
አምር ዘንተ ወአዘዘ የሀብዋ ዘትበልዕ ።

### ምዕራፍ ፮፤

### ክፍል ፡ ፳ወ፫ በእንተ ስብከቱ በናዝሬት ።

፩ ወወፅአ እምህየ በአ ሀገሮ ወተለውዎ አርዳኢሁ ።
፪ ወበሰንበት መሀሮሙ በምኵራብ ወብዙኃን ያፀም
እዎ ወያነክሩ እንዘ ይብሉ እምአይቴ ሎቱ ዝንቱ
ኵሉ ትምህርት ወምንትኑ ዛቲ ጥበብ እንተ ተውህ
በት ሎቱ ወዝኒ ኃይል ዘይትገበር በእደዊሁ ።
፫ አኮኑ ዝንቱ ውእቱ ወልዱ ለፀራቢ ወወልደ ማር
ያም ወአኀዊሁኒ ያዕቆብ ወዮሳ ወይሁዳ ወስምዖን
ወአኮኑ አኃቲሁኒ ሀለዋ ዝየ ኀቤነ ወተዐቀፉ በእ
ንቲአሁ ።
፬ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ኢኮነ ምኑነ ነቢይ
ዘእንበለ በሀገሩ ወበቤቱ ወበኀበ አዝማዲሁ ።
፭ ወኢገብረ ኃይለ በህየ ዘእንበለ ለኅዳጣን ድዉያን
እለ አንበረ እዴሁ ዲቤሆሙ ወአሕየዎሙ ።
፮ ወአንከረ ኢአሚኖቶሙ ወአንሶሰወ ውስተ አህጉረ
አድያም እንዘ ይሜህር ።

## የማርቆስ ወንጌል ፭ ።

ልጄ ! ሃይማኖትሽ አዳነችሽ ፡ ከደዌሽም ተፈወሺና ፴፬
በሰላም ወደ ቤትሽ ግቢ አላት ።
ከእርሷ ጋር ሲነጋገርም ከምኵራብ ሹሙ ቤት ፴፭
ሰዎች መጥተው ልጅህ ሞታለች ፡ አንግዲህ መምህ
ርን አታድክመው አሉት ።
ጌታ ኢየሱስም ሲያነጋግሩት ሰምቶ የምኵራቡን ፴፮
ሹም አትፍራ ፡ ብቻ እመን አለው ።
ከጴጥሮስ ፡ ከያዕቆብና ፡ ከያዕቆብ ወንድም ከዮሐንስ ፴፯
በቀር የሚከተለው እንዳይኖር ከለከለ ።
ወደ ምኵራቡ ሹም ቤትም በገባ ጊዜ ሲሸበሩ ሲያ ፴፰
ለቅሱ ዋይ ዋይ ሲሉ አገኛቸው ።
ገብቶም ለምን ትሸበራላችሁ ? ለምንስ ታለቅሳላ ፴፱
ችሁ ? ልጅቱ አልሞተችም ተኝታለች እንጂ ! እነ
ርሱም ሳቁበት ። ዮሐ ፲፩ ፡ ፲፩ ።
ከዚህ በኋላ ሁሉንም አስወጥቶ የሕፃኒቱን አባትና ፵
እናት ከእሱ ጋር የነበሩትንም ይዟቸው ብላቴናዪቱ
ወደ አለችበት ገባ ።
የብላቴናዪቱንም እጅዋን ይዞ ጣቢታ ቁሚ አላት ፵፩
ትርጓሜውም ልጄ ሆይ ተነሺ ማለት ነው ። ሉቃ
፯ ፡ ፲፬ ።
ያን ጊዜም ያቺ ብላቴና ተነሥታ ወዲያና ወዲህ ፵፪
አለች ፡ ዕድሜዋም ዐሥራ ሁለት ዓመት ነበር ታላቅ
ድንጋፄም ደነገጡ ።
ይህንንም የሚያውቅ እንዳይኖር እናት አባቷን ፵፫
በብዙ መከራቸው ፡ የምትበላውም እንዲሰጧት አዘዘ ።

### ምዕራፍ ፮፤

### ክፍል ፳፫ ፡ በናዝሬት ስለ ማስተማሩ ።

ከዚያም ወጥቶ ወደ ሀገሩ ገባ ፡ ደቀ መዛሙርቱም ፩
ተከተሉት ። ማቴ ፲፫ ፡ ፶፫ - ፶፰ ። ሉቃ ፬ ፡ ፲፭ - ፴ ።
በሰንበትም በምኵራብ አስተማራቸው ብዙዎችም ፪
እያደነቁ ይህ ሁሉ ትምህርት ከየት ተገኘለት ?
ይህች ለእርሱ የተሰጠች ዕውቀትስ ምንድር ናት ?
ይህ በእጁ የሚደረገውስ ኃይል ምንድር ነው ?
እያሉ ያደንቁ ነበር ። ዮሐ ፯ ፡ ፲፭ ።
ይህ የፀራቢው ልጅ የማርያም ልጅ አይደለምን ? ፫
ያዕቆብ ፡ ዮሳ ፡ ይሁዳና ስምዖንስ ወንድሞቹ አይደ
ሉምን ? እኅቶቹስ ሁሉ ከእኛ ዘንድ ያሉ አይደ
ለምን ? እያሉ በእርሱ ነገር ተሰናከሉ ።
ጌታ ኢየሱስም ነቢይ በሀገሩ በወገኑ በዘመዶቹ ፬
ዘንድ ነው እንጂ ፡ በሌላ የሚናቅ አይደለም ።
እጁን ጭኖ ከአዳናቸው ከጥቂት ድውያንም በቀር ፡ ፭
በዚያ ተአምራት አላደረገም ።
አለማመናቸውንም አደነቀ ፡ እያስተማረም በአውራ ፮
ጃው ሀገሮች ሁሉ ተዘዋወረ ።

## ክፍል ፳ወ፬ ፡ በእንተ ፈንዎቶ ሐዋርያተ ይስብኩ ።

፯ ወጸውዖሙ ለዐሠርቱ ወክልኤቱ ሐዋርያት ወፈ
ነዎሙ በበክልኤቱ ወአብሐሙ ላዕለ አጋንንት
እኩያን ።
፰ ወአዘዘሙ ከመ አልቦ ዘይሰንቁ ወኢይንሥኡ ለፍ
ኖት ዘእንበለ በትር ባሕቲታ ወኢኅብስተ ወኢጽፍ
ነተ ወኢጸሬቀ ውስተ ቅናቶሙ ።

፱ ዘእንበለ አሣእን ዘውስተ እገሪሆሙ ወኢይልበሱ
ክልኤ ክዳናተ ።
፲ ወይቤሎሙ ቤተ ኀበ በእክሙ ሀየ ንበሩ እስከ አመ
ትወፅኡ እምህየ ።
፲፩ ወብሔረ ኀበ ኢተወክፉክሙ ወኢሰምዑክሙ ወፂ
አክሙ እምህየ ንግፉ ጸበለ እገሪክሙ ከመ ይኩን
ስምዐ ላዕሌሆሙ ፡ አማን እብለክሙ ከመ ይረክበ
ሳሕተ ሰዶም ወገሞራ አመ ዕለተ ደይን እምይእቲ
ሀገር ።
፲፪ ወወፂአሙ ሰበኩ ውስተ ኵሉ አህጉር ከመ ኵሉ
ይነስሑ ።
፲፫ ወብዙኃነ አጋንንተ ያወፅኡ ወይቀብእዎሙ ቅብአ
ለብዙኃን ድውያን ወየሐይዉ ።

## ክፍል ፳ወ፭ ፡ በእንተ ዮሐንስ ወሄሮድስ ።

፲፬ ወሰሚዖ ሄሮድስ ንጉሥ እስመ ክሡተ ኮነ ስሙ
ወይቤ ዮሐንስ መጥምቅ ተንሥአ እሙታን ወበ
እንተዝ ይረድኦ ኃይል ።
፲፭ ወበ እለ ይቤሉ ኤልያስ ውእቱ ወበ እለ ይቤሉ
ነቢይ ውእቱ ወእመ አኮ ይቤሉ ከመ አሐዱ እም
ነቢያት ።
፲፮ ወሰሚዖ ሄሮድስ ይቤ ዮሐንስ ውእቱ ዘአነ መት
ርኩ ርእሰ ውእቱ ተንሥአ እሙታን ።
፲፯ እስመ ውእቱ ሄሮድስ ፈነወ አግብርቲሁ ወአኀዘ
ለዮሐንስ ወሞቅሖ በእንተ ሄሮድያዳ ብእሲተ ፊል
ጶስ እኁሁ እስመ ኪያሃ አውሰበ ።
፲፰ እስመ ይቤሎ ዮሐንስ ኢይከውነከ ታውስብ ብእ
ሲተ እኁከ ።
፲፱ ወተቀየመቶ ሄሮድያዳ ወፈቀደት ትቅትሎ ወስእነት ።

፳ ወኮነ ይፈርሆ ሄሮድስ ለዮሐንስ እስመ የአምር
ከመ ብእሲ ጻድቅ ወቅዱስ ውእቱ ወይትዐቀበ ወብ
ዙኀ ይሰምዕ በኀቤሁ ወይፈቅድ ይርአይ ተአምረ
ዘይገብር ወያስተሐውዝ ወይፈቅድ ይስምዮ ።
፳፩ ወኮነት ዕለት አመ ይገብር ሄሮድስ በዓለ ዘዕለተ
ተወልደ ወአምስሐ መኳንንቲሁ ወመላእክቲሁ ወመ
ሳፍንቲሁ ወመገብቶ ወዓበይተ ሀገረ ገሊላ ።





## ክፍል ፳፬ ፡ ያስተምሩ ዘንድ ሐዋርያትን ስለ መላኩ ።

ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ጠርቶ ሁለት ሁለት አድ ፯
ርጎ ላካቸው ፡ በክፉዎች አጋንንት ላይም ሥልጣን
ሰጣቸው ። ሉቃ ፲ ፡ ፩ - ፯ ። ማቴ ፲ ፡ ፩ - ፱ ።
ለመንገድም ከብትር በቀር ስንቅ እንዳይዙ አዘዛ ፰
ቸው ፡ እንጀራም ቢሆን የስንቅ ስልቻም ቢሆን ፡
መሐለቅም ቢሆን በመቀነታቸው እንዳይቋጥሩ አዘ
ዛቸው ።
በእግራቸውም ካለው ጫማ በቀር ሁለት ልብስ እን ፱
ዳይለብሱ አዘዛቸው ።
ከዚያ እስክትወጡ ድረስ ከገባችሁበት ቤት ከዚ ፲
ያው ተቀመጡ አላቸው ።
ካልሰሟችሁ ካልተቀበሏችሁ ሀገርም ከዚያ ወጥታ ፲፩
ችሁ የእግራችሁን ትቢያ አራግፉ ፡ ምስክር ሊሆን
ባቸው ፡ ከዚያች ሀገር ይልቅ በፍርድ ቀን ሰዶም
ገሞራ ዕረፍትን እንዲያገኙ በውነት እነግራችኋለሁ ።
ማቴ ፲ ፡ ፲፬ ።
ወጥተውም ሁሉ ንስሐ ይገቡ ዘንድ በያውራጃው ፲፪
አስተማሩ ።
ብዙ አጋንንትን ያወጡ ነበር ብዙ ድውያንንም ፲፫
ዘይት እየቀቡቸው ይድኑም ነበር ። ያዕ ፭ ፡ ፲፬ ።

## ክፍል ፳፭ ፡ ስለ ዮሐንስና ስለ ሄሮድስ ።

ንጉሥ ሄሮድስም ስሙ እንደ ተጋነነ ሰምቶ ፡ ዮሐ ፲፬
ንስ መጥምቅ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ፡ ስለዚህም
ኃይል ይረዳዋል አለ ። ማቴ ፲፬ ፡ ፩ - ፲፪ ።
ኤልያስ ነው ያሉም አሉ ፡ ነቢይ ነው ያም ባይሆን ፲፭
ከነቢያት እንደ አንዱ ነው ያሉም አሉ ። ሉቃ ፱፡፯-፱።

ሄሮድስ ግን ሰምቶ ይህ እኔ ራሱን ያስቈረጥኩት ፲፮
ዮሐንስ ነው ፡ እርሱ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ አለ ።
እርሱ ሄሮድስ ስለ አገባት ስለ ወንድሙ ስለ ፊልጶስ ፲፯
ሚስት ስለ ሄሮድያዳ ጭፍሮቹን ልኮ ዮሐንስን ይዞ
አሥሮት ነበርና ።
ዮሐንስ የወንድምህን ሚስት ልታገባ አይገባህም ፲፰
ብሎታልና ። ዘሌ ፲፰ ፡ ፲፯ ።
ሄሮድያዳም ተቀይማው ልትገድለው ትወድ ነበር ፲፱
ግን አልተቻላትም ነበር ።
ሄሮድስ ግን ዮሐንስን ፡ ጻድቅ ቅዱስ ሰው እንደሆነ ፳
ያውቅ ነበርና ይፈራውና ይጠባበቀው ነበር ፡ ከእር
ሱም ብዙ ይማር ስለ ነበር የሚያደርገውን ተአም
ራት ሊያይ ፡ ደስ እያለውም ሊሰማው ይወድ ነበረ ።
ሄሮድስ የተወለደበትን ቀን በዓል የሚያከብርበት ፳፩
ዕለት ስለ ነበረ ፡ መኳንንቱን አለቆቹን መሳፍንቱን
ሹማምንቱን በገሊላ ሀገር ያሉትን ታላላቅ ሰዎች
ግብር አግብቶ አበላ ።

## ወንጌል ዘማርቆስ ፮ ።

፳፪ ወቦአት ወለተ ሄሮድያዳ ወዘፈነት ሎቱ ወአሥመ
ረቶ ለሄሮድስ ወለእለ ይረፍቁ ምስሌሁ ፥ ወይቤላ
ንጉሥ ለይእቲ ወለት ሰአልኒ ዘትፈቅዲ ወእሁበኪ ።

፳፫ ወመሐለ ላቲ ከመ የሀባ ዘሰአለቶ እስከ መንፈቀ
መንግሥቱ ።
፳፬ ወወፅአት ወትቤላ ለእማ ምንተ እስአሎ ፥ ወትቤላ
ርእሰ ለዮሐንስ መጥምቅ ።
፳፭ ወቦአት ሶቤሃ ኀበ ንጉሥ እንዘ ትጔጕእ ወሰአለቶ
ወትቤሎ እፈቅድ ይእዜ ተሀበኒ ርእሰ ለዮሐንስ
መጥምቅ በፃሕል ።
፳፮ ወተከዘ ንጉሥ በእንተ መሐላሁ ወበእንተሂ እለ
ይረፍቁ ምስሌሁ ወኢፈቀደ ይእበያ ።
፳፯ ወፈነወ ንጉሥ ሶቤሃ መስተራትዓተ ሐራ ወአዘዘ
ያምጽኡ ርእሶ ።
፳፰ ወሖሩ ወመተሩ ርእሶ ለዮሐንስ መጥምቅ በቤተ
ሞቅሕ ወአምጽኡ ርእሶ በፃሕል ወወሀብዋ ለይእቲ
ወለት ፥ ወይእቲኒ ወለት ወሀበት ለእማ ።
፳፱ ወሰሚዖሙ አርዳኢሁ ሖሩ ወነሥኡ በድኖ ለዮ
ሐንስ ወቀበርዎ ።

### ክፍል ፳ወ፮ ፥ በእንተ ተመይጠቶሙ ሐዋርያት ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ።

፴ ወተጋብኡ ሐዋርያት ኀበ እግዚእ ኢየሱስ ወነገርዎ
ኵሎ ዘገብሩ ወዘከመ መሀሩ ።
፴፩ ወይቤሎሙ ንዑ ንፃእ ገዳመ ባሕቲትነ ወታዕርፉ
ሕቀ እስመ ብዙኃን እለ የሐውሩ ወይመጽኡ ወኢ
ያበውሕዎሙ ይብልዑ እክለ ወኢያስተርክቡ ።
፴፪ ወሖሩ ሐቅለ በሐመር ባሕቲቶሙ ።

፴፫ ወርእይዎሙ እንዘ የሐውሩ ወአእመርዎሙ ብዙ
ኃን ወሖሩ እንተ እግር ኀቤሁ እምኵሉ አህጉር
ወተቃደምዎሙ ወመጽኡ ኀቤሁ ።

### ክፍል ፳ወ፯ ፥ በእንተ ባርኮቱ ኃምሰ ኅብስተ ወ፪ኤተ ዓሣተ ።

፴፬ ወወፂኦ እግዚእ ኢየሱስ ርእየ ብዙኃነ ሰብአ ወም
ሕሮሙ እስመ ከመ አባግዕ ዘአልቦ ኖላዊ እሙንቱ
ወአኀዘ ይምሀሮሙ ብዙኃ ።
፴፭ ወእምድኅረ ብዙኅ ሰዓት መጽኡ አርዳኢሁ ወይቤ
ልዎ ሐቅል ውእቱ ዝ ብሔር ወሰዓቱኒ ወድአ መስየ ።

፴፮ ሠዐር ሰብአ ይሑሩ ውስተ አህጉር ወአዕፃዳት
ወይሣየጡ ሎሙ ሲሳየ እስመ አልቦሙ ዘይበልዑ ።
፴፯ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ሀብዎሙ አንትሙ ዘይበ
ልዑ ወይቤልዎ ንሑርኑ ንሣየጥ በክልኤ ምእት
ዲናር ኅብስተ ወነሀቦሙ ይብልዑ ።

## የማርቆስ ወንጌል ፮ ።

የሄሮድያዳ ልጅም ወደ አዳራሹ ገብታ ዘፈነችለትና ፳፪
ሄሮድስን ደስ አሰኘችው ፥ ከእሱ ጋር በግብር ላይ
የነበሩትንም ደስ አሰኘቻቸው ፥ ንጉሡም የምትሺ
ውን ለምኚኝ እሰጥሻለሁ አላት ።
እስከ መንግሥቱ እኩሌታ ድረስም ቢሆን የለመነች ፳፫
ውን ሊሰጣት ማለላት ። አስቴ ፭ ፥ ፫ - ፮ ።
ወጣ ብላም እናቷን ምን ልለምነው ? አለቻት ፥ የመ ፳፬
ጥምቁ የዮሐንስን ራስ ነዋ ! አለቻት ።
ያን ጊዜም እየሮጠች ወደ ንጉሡ ገብታ የመጥም ፳፭
ቁን የዮሐንስን ራስ በወጭት አሁን እንድትሰጠኝ
እሻለሁ ብላ ለመነችው ።
ንጉሡም ስለ መሐላው አብረዉት ስለ ነበሩትም ፳፮
አዘነ ፥ እንቢ ሊላት ግን አልወደደም ።
ያን ጊዜም ንጉሥ ራሱን እንዲያመጡ አዝዞ የጭፍ ፳፯
ሮቹን ባለወጎች ላከ ።
ሂደውም የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ በግዞት ቤት ፳፰
ቈርጠው ራሱን አመጡና ለዚያች ብላቴና ሰጧት ፥
እሷም ለእናቷ ሰጠች ።
ደቀ መዛሙርቱም በሰሙ ጊዜ ሄዱና የዮሐንስን ፳፱
በድን ወስደው ቀበሩት ።

### ክፍል ፳፮ ፥ ሐዋርያት ወደ ጌታ ስለ መመለሳቸው ።

ሐዋርያትም ወደ ጌታ ኢየሱስ ተሰብስበው ያደረጉ ፴
ትንና ያስተማሩትን ሁሉ ነገሩት ። ሉቃ ፲ ፥ ፱ ።
ኑ ለብቻችን ወደ ምድረ በዳ እንውጣና ጥቂት ዕረፉ ፴፩
አላቸው ፥ የሚመጡ የሚሄዱ ብዙዎች ነበሩና እህል
ይበሉ ዘንድ ፋታ አልሰጧቸውም ጊዜ አላገኙምና ።
ብቻቸውንም በመርከብ ወደ ጫካ ሄዱ ። ማቴ ፲፬ ፥ ፴፪
፲፫ - ፳፩ ። ሉቃ ፱ ፥ ፲፩ - ፲፯ ። ዮሐ ፮ ፥ ፩ - ፲፫ ።
ብዙዎቹም ሲሄዱ አይተው አወቋቸው ከሀገሩም ፴፫
ሁሉ በእግር ወደርሱ ሄዱ ቀድመዋቸውም ወደርሱ
መጡ ።

### ክፍል ፳፯ ፥ ሁለቱን ዓሣዎችና አምስቱን እንጀራ ስለ መባረኩ ።

ጌታ ኢየሱስም በመጣ ጊዜ ብዙ ሰዎችን አየና አዘ ፴፬
ነላቸው እረኛ እንደሌላቸው በጎች ነበሩና ፥ ብዙም
ያስተምራቸው ጀመር ። ማቴ ፱ ፥ ፴፮ ።
ከብዙ ሰዓት በኋላም ደቀ መዛሙርቱ መጥተው እን ፴፭
ዲህ አሉት ፥ ይህ ሥፍራ በረኻ ነው ጊዜውም
ፈጽሞ መሽቷል ። ምዕ ፰ ፥ ፩ - ፲ ።
ሕዝቡን ወደ አገር ወደ መንደር ሂደው ምግባቸ ፴፮
ውን ይገዙ ዘንድ አሰናብት የሚበሉት የላቸውምና ።
እርሱም መልሶ እናንተ የሚበሉትን ስጧቸው አላ ፴፯
ቸው ፥ እርሱም እንሂድና በሁለት ወቄት እንጀራ ገዝ
ተን ይበሉ ዘንድ እንስጣቸውን ? አሉት ።

ድዉያነ በዓራታት ወይወስዱ ኀበ ሰምዑ ከመ ሀሎ
ውእቱ ሀየ ።
፶፮ ወውስተ አህጉር ወአዕፃዳት ወውስተ ምሥያጣት
ኀበ በአ ያነብርዎሙ ለድውያን ወያስተበቍዕዎ
ከመ ይግሥሡ ጽንፈ ልብሱ ወኵሎሙ እለ ገሠ
ሥዎ የሐይዉ ።

ምዕራፍ ፯ ፤

<u>ክፍል ፴ ፡ በእንተ ፈሪሳውያን ወሥርዓቶሙ ።</u>

፩ ወተጋብኡ ኀቤሁ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን መጺኦሙ
እምኢየሩሳሌም ።
፪ ወርእይዎሙ ለአርዳኢሁ እንዘ ይበልዑ እክለ ዘእ
ንበለ ይትሐጸቡ እደዊሆሙ ።
፫ እስመ ፈሪሳውያንሰ ወኵሎሙ አይሁድ ለእመ በሕቁ
ኢተሐፅቡ እደዊሆሙ ኢይበልዑ እክለ እስመ የዓ
ቅቡ ሥርዓቶሙ ለረበናት ።
፬ ወዘሂ ተሣየጡ እምሥያጥ ኢይበልዑ ለእመ ኢያ
ጥመቅዎ በማይ ወባዕደኒ ብዙኀ ሕርመተ ይትዐቀቡ
ወያጠምቁ ጽዋዓተኒ ወቈሳቍሳተኒ ወጽሕርታተኒ
ወዓራታተኒ ።
፭ ወይቤልዎ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን ለምንት ኢየሐ
ውሩ አርዳኢከ በከመ ሠርዑ ረበናት ወዘእንበለ
ይትሐፀቡ እደዊሆሙ ይበልዑ እክለ ።
፮ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ አ መደል
ዋን ሠናየ ተነበየ ኢሳይያስ ላዕሌክሙ እንዘ ይብል
ዝንቱ ሕዝብ በከናፍሪሆሙ ያከብሩኒ ወበልበሙሰ
ነዋኃ ይርኅቁ እምኔየ ።
፯ ወከንቶ ያመልኩኒ እንዘ ይሜህሩ ሥርዓታተ ትእ
ዛዛተ ሰብእ ።
፰ ወየኃድጉ ትእዛዘ እግዚአብሔር ወየዓቅቡ ትእዛ
ዛተ እጓለ እመሕያው ጥምቀታተ ጽዋዓት ወቈሳቍ
ሳት ፡ ወጽሕርታት ፡ ወባዕደኒ ብዙኀ ዘይመስሎ ለዝ
ንቱ ።
፱ ወይቤሎሙ ርቱዕኑ ትዕልዉ ትእዛዘ እግዚአብሔር
ከመ ትዕቀቡ ትእዛዘ ርእስክሙ ።
፲ ወሙሴ ይቤለክሙ "አክብር አባከ ወእመከ ወዘአኅ
ሰመ ቃለ ላዕለ አቡሁ ወእሙ ሞተ ለይሙት" ።
፲፩ ወአንትሙሰ ትብሉ ዘይቤሎ ለአቡሁ አው ለእሙ
ቍርባን ዘረባኅከ እምኔየ ብሂል ።
፲፪ ኢታበውሕዎ ይግበር ምንተኒ ለአቡሁ ወለእሙ ።
፲፫ ወትሥዕሩ ቃለ እግዚአብሔር በእንተ ትእዛዝ ዘሠ
ራዕክሙ ወዓዲ ብዙኀ በአምሳለ ዝንቱ ዘትገብሩ ።
፲፬ ወጸውዖሙ ካዕበ ለሕዝብ ወይቤሎሙ ስምዑ ኵል
ክሙ ወለብዉ ።
፲፭ ወአልቦ ዘይበውእ እምአፍአ ውስተ አፉሁ ለሰብእ



እርሱ ከዚያ እንዳለ ወደ ሰሙበት ቦታ ይወስዷቸው
ነበር ።
በየአገሩ በየመንደሩ በየከተማው በገባበት ሁሉ ፶፮
ድዉያኑን ያስቀምጡና የልብሱን ጫፍ እንዲዳሥሡ
ይለምኑት ነበር ፡ የዳሠሡትም ሁሉ ይድኑ ነበር ።
ምዕ ፭ ፡ ፳፯ - ፳፰ ።

ምዕራፍ ፯ ፤

<u>ክፍል ፴ ፡ ስለ ፈሪሳውያንና ስለ ሥርዓታቸው ።</u>

ጻፎችና ፈሪሳውያንም ከኢየሩሳሌም መጥተው ወደ ፩
ርሱ ተሰበሰቡ ። ማቴ ፲፭ ፡ ፩ - ፳ ።
ደቀ መዛሙርቱም እጃቸውን ሳይታጠቡ እንጀራ ፪
ሲበሉ አዩአቸው ። ሉቃ ፲፩ ፡ ፴፰ ።
ፈሪሳውያንና አይሁድ የሽማግሌዎችን ወግ ስለሚጠ ፫
ብቁ እጃቸውን በጣም ካልታጠቡ እህል አይበሉም
ነበርና ።
ከገበያ የገዙትንም በውኃ ካላጠቡ አይበሉም ነበር ፡ ፬
ሌላም ብዙ ጥንቃቄ ይጠነቀቁ ነበር ፡ ጽዋዉን ኵስ
ኵስቱን ድስቱን አልጋዉን የቤት ዕቃ ሁሉ ያጥቡ
ነበር ።
ጻፎችና ፈሪሳውያንም ደቀ መዛሙርትህ ለምን እንደ ፭
ሽማግሌዎች ወግ አይሄዱም ፡ እጃቸውን ሳይታጠቡ
ለምን እህል ይበላሉ ? አሉት ።
ጌታ ኢየሱስም መለሰና እንዲህ አላቸው ፡ እናንተ ግብ ፮
ዞች ኢሳይያስ በእናንተ ላይ በሚገባ ተናግሯል እን
ዲህ ብሎ ፡ "ይህ ሕዝብ በከንፈራቸው ያከብሩኛል ፡
በልባቸው ግን ከእኔ እጅግ ይርቃሉ" ። ኢሳ ፳፱ ፡ ፲፫ ።
የሰው ሥርዓት የሆነ ትምህርትንም እያስተማሩ በከ ፯
ንቱ ያመልኩኛል ። ኢሳ ፳፱ ፡ ፲፫ ።
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትተው የሰውን ትእዛዝ ፰
ይጠብቃሉ ፡ ጽዋውን ፡ መንቀሉን ፡ ድስቱንም ፡ የቤት
ዕቃውን ሌላውንም ይህን የመሰለውን ብዙ ማጠብን
ይጠብቃሉ ።
ደግሞ እንዲህ አላቸው ፡ የራሳችሁን ትእዛዝ ጠብ ፱
ቃችሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ታፈርሱ ዘንድ አገ
ባብ ነውን ?
ሙሴም "አባትህንና እናትህን አክብር ፡ በአባቱና በእ ፲
ናቱ ላይ ክፉ ቃል የተናገረ ሞትን ይሙት ብሏችሁ
ነበር" ። ዘፀ ፳ ፡ ፲፪ ። ዘሌ ፳ ፡ ፱ ። ዘዳ ፭ ፡ ፲፮ ። ኤፌ ፮ ፡ ፪ ።
እናንተ ግን አባቱን ወይም እናቱን ያለውን ከእኔ ፲፩
የምትጠቀምበት ቍርባን ማለት ነው ትላላችሁ ።
ለአባቱና ለእናቱ ምንም እንዲሠራ አታደርጉትም ። ፲፪
ስለ ሠራችሁት ሥርዓት የእግዚአብሔርን ቃል ትሽ ፲፫
ራላችሁ በዚህም ዓይነት የምትሠሩት ብዙ ነው ።
ዳግመኛም ሕዝቡን ጠርቶ እንዲህ አላቸው ፡ ሁላች ፲፬
ሁም ስሙ አስተውሉ ።
ከውጭ ወደ ሰው አፍ የሚገባው ሊያረክሰው የሚ ፲፭

፲፰

## ወንጌል ዘማርቆስ ፰ ።

፳፰ ወይቤልዎ ዮሐንስሃ መጥምቀ፡ አው ኤልያስሃ፡
አው አሐዱ እምነቢያት ።
፳፱ ወይቤሎሙ አንትሙኬ መነ ትብሉኒ፡ ወተሰጥዎ
ጴጥሮስ ወይቤሎ አንተ ውእቱ ክርስቶስ ።
፴ ወገሥፆሙ ከመ ኢይንግሩ ወኢለመኑሂ ።
፴፩ ወኣኀዘ ይምሀሮሙ ከመ ሀለዎ ለወልደ እጓለ እመ
ሕያው ብዙኀ ያሕምምዎ ወያመክርዎ ረበናት ወሊ
ቃነ ካህናት ወጸሐፍት ወይቀትልዎ ወይትነሣእ
በሣልስት ዕለት ።
፴፪ ወገሀደ ይነግሮሙ ዘንተ ነገረ፡ ወቀርበ ጴጥሮስ
ወአኀዘ ይገሥፆ ።
፴፫ ወተመይጠ ወነጸረ ኀበ አርዳኢሁ ወገሥፆ ለጴጥሮስ
ወይቤሎ ሑር እምድኅሬየ ሰይጣን እስመ ኢትሔሊ
ዘእግዚአብሔር ዘእንበለ ዘእጓለ እመሕያው ።

### ክፍል ፴ወ፰፡ በእንተ ተፀምዶት ለእግዚእ ኢየሱስ ።

፴፬ ወጸውዖሙ ለሕዝብ ምስለ አርዳኢሁ ወይቤሎሙ
ዘይፈቅድ ይጸመደኒ ይጽልእ ለነፍሱ ወያጥብእ
ወይንሣእ መስቀለ ሞቱ ወይትልወኒ ።
፴፭ ወዘይፈቅድ ያድኅና ለነፍሱ ለይግድፋ፡ ወዘሰ ገደፋ
ለነፍሱ በእንቲአየ ወበእንተ ወንጌል ይረክባ ።
፴፮ ወምንተ ይበቍዖ ለሰብእ ለእመ ኮሎ ዓለመ ረብኀ
ወነፍሶ ኀጕለ ።
፴፯ ወምንተ እምወሀበ ሰብእ ቤዛሃ ለነፍሱ ።
፴፰ ወለዘኒ ኀፈረኒ ወኀፈረ ቃልየ በዛቲ ትውልድ ዘማ
ወኃጥእት ወልደ እጓለ እመሕያውኒ የኀፍሮ አመ
ይመጽእ በስብሐተ አቡሁ ምስለ መላእክቲሁ
ቅዱሳን ።

### ምዕራፍ ፱፤

፩ ወይቤሎሙ አማን እብለክሙ ሀለዉ እምእለ ይቀ
ውሙ ዝየ እለ ኢይጥዕምዎ ለሞት እስከ አመ
ይሬእይዎ ለመንግሥተ እግዚአብሔር እንዘ ትመጽእ
በኀይል ።

### ክፍል ፴ወ፱፡ በእንተ አስተርእዮተ

### ስብሐቲሁ በደብረ ታቦር ።

፪ ወእመ ሰዱስ ዕለት ነሥኦሙ እግዚእ ኢየሱስ ለጴ
ጥሮስ ወለያዕቆብ ወለዮሐንስ ወአዕረጎሙ ደብረ
ነዋኀ በባሕቲቶሙ ወተወለጠ ራእዩ በቅድሜሆሙ ።

፫ ወአልባሲሁኒ በረቀ ወፃዕደወ ጥቀ ወኢይክል መሐ
ፒል ከማሁ አፃዕድዎቶ በዲበ ምድር ።

፬ ወአስተርአይዎሙ ሙሴ ወኤልያስ እንዘ ይትናገሩ
ምስለ እግዚእ ኢየሱስ ።

## የማርቆስ ወንጌል ፰ ።

ዮሐንስ መጥምቅን ያም ባይሆን ኤልያስን ወይም ፳፰
ከነቢያት አንዱ ነው፡ ይሉሃል አሉት ። ምዕ ፮፡ ፲፭ ።
እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ? አላቸው፡ ጴጥሮስም ፳፱
መልሶ አንተ ክርስቶስ ነህ አለው ።
ለማንም ለማን እንዳይናገሩ አዘዛቸው ። ምዕ ፱፡ ፱ ። ፴
ሽማግሎች፡ የካህናት አለቆችና ጻፎች ወልደ እጓለ ፴፩
እመሕያውን ይፈትኑት ብዙ መከራ ያጸኑበት ዘንድ
ይገድሉት ዘንድ እንዳለውና፡ በሦስተኛውም ቀን
እንደሚነሣ ያስተምራቸው ጀመር ።
ይህንንም ነገር በግልጥ ይነግራቸው ጀመረ፡ ጴጥሮ ፴፪
ስም ቀረብ ብሎ ይመክረው ጀመረ ።
መለስ ብሎ ወደ ደቀ መዛሙርቱ አየና የሰውን ፴፫
እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ሰይጣን ከኋላዬ
ሂድ ብሎ ጴጥሮስን ገሠፀው ።

### ክፍል ፴፰፡ ጌታ ኢየሱስን ስለ ማገልገል ።

ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ሕዝቡን ጠርቶ እንዲህ ፴፬
አላቸው፡ "ሊያገለግለኝ የሚወድ ሰውነቱን ይጥላት
ጨክኖም የሞትን መከራ ተቀብሎ ይከተለኝ" ።
ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ይጣላት ስለ እኔና ስለ ፴፭
ወንጌል የጣላት ሰውነቱን ያገኛታል ። ማቴ ፲፡ ፴፱ ።
ዓለሙን ሁሉ ቢገዛ ነፍሱን ቢያጣ ለሰው ምን ይጠ ፴፮
ቅመዋል?
ወይስ ሰው የነፍሱን ቤዛ ምን በሰጠ? ፴፯
በዚች ኃጢአተኛና አመንዝራ ትውልድ ያፈረኝ፡ ፴፰
በቃሌም ያፈረውን የሰው ልጅም በአባቱ ክብር
ከቅዱሳን መላእክት ጋር በመጣ ጊዜ ያፍረዋል ።
ማቴ ፲፡ ፴፫ ።

### ምዕራፍ ፱፤

እውነት እላችኋለሁ እዚህ ከቆሙት የእግዚአብሔ ፩
ርን መንግሥት በኃይል መጥታ እስኪያዩዋት ድረስ
ሞትን የማይቀምሷት አሉ አላቸው ።

### ክፍል ፴፱፡ በደብረ ታቦር

### ጌትነቱን ስለ መግለጡ ።

በስድስተኛው ቀን ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስን ያዕቆ ፪
ብንና ዮሐንስን ለብቻቸው ወስዶ ወደ ረዥም ተራራ
አወጣቸው፡ መልኩም በፊታቸው ተለወጠ ። ማቴ
፲፯፡ ፩ - ፲፫ ። ሉቃ ፱፡ ፳፰ - ፴፮ ።
ልብሱም እጅግ ነጭ ሆነ፡ ተብረቀረቀ፡ ሸማ አጣቢ ፫
በምድር ላይ እንደዚያ ዓይነት አድርጎ ሊያነፃ አይ
ችልም ።
ሙሴና ኤልያስ ከጌታ ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ ታዩ ፬
አቸው ።

፭ ወአውሥአ ጴጥሮስ ወይቤሎ ለእግዚእ ኢየሱስ
ረቢ ይኄይሰነ ንንበር ዝየ ወንግበር ሠለስተ ማኅደረ፡
አሐደ ለከ፡ ወአሐደ ለሙሴ፡ ወአሐደ ለኤልያስ ።
፮ ወኢየአምር ዘይብል እስመ ድንጉፃን እሙንቱ ።
፯ ወመጽአ ደመና ብሩህ ወጸለሎሙ ወመጽአ ቃል
እምደመና ዘይብል "ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈ
ቅር ወሎቱ ስምዕዎ" ።
፰ ወእምዝ ግብተ ነጺሮሙ አልቦ ዘርእዩ ዘእንበለ
እግዚእ ኢየሱስ በሕቲቱ ምስሌሆሙ ።

፱ ወእንዘ ይወርዱ እምደብር አዘዞሙ እግዚእ ኢየ
ሱስ ኢይንግሩ ወኢለመኑሂ ዘርእዩ ዘእንበለ እመ
ተንሥአ ወልደ እጓለ እመሕያው እምነ ምዉታን ።

፲ ወዐቀቡ ቃሎ ወተኃሠሡ በበይናቲሆሙ እንዘ
ይብሉ ምንት ውእቱ ተንሥኦ እምነ ምዉታን ።
፲፩ ወተስእልዎ ወይቤልዎ በእፎ ይብሉ ጸሐፍት ወፈ
ሪሳውያን ኤልያስ ይቀድም መጺአ ።
፲፪ ወአውሥአ ወይቤሎሙ ኤልያስ ይመጽእ ቅድመ
ወያስተራትዕ ኵሎ ወእፎ ጽሑፍ በእንተ ወልደ
እጓለ እመሕያው ከመ ብዙኀ ያሐምምዎ ወይ
ሜንንዎ ።
፲፫ ወባሕቱ እብለክሙ ኤልያስ ወድአ መጽአ ወገብሩ
ላዕሌሁ ኵሎ ዘፈቀዱ በከመ ጽሑፍ በእንቲአሁ ።

፲፬ ወበጽሐ ኀበ አርዳኢሁ ወረከበ ብዙኀ ሰብአ ኀቤ
ሆሙ ወጸሐፍትኒ እንዘ ይሴአልዎ ።

፲፭ ወሶበ ርእይዎ ኵሎሙ ሰብእ ደንገፁ ወሮፁ ሶቤሃ
ወአምኅዎ ።
፲፮ ወተስእሎሙ ለጸሐፍት እንዘ ይብል ምንተኑ ትትኀ
ሠሥዎሙ ።

## ክፍል ፵፡ በእንተ ዘነገርጋር ።

፲፯ ወአውሥአ አሐዱ እምውስተ ሕዝብ ወይቤሎ ሊቅ
አምጻእክዎ ለወልድየ ኀቤከ እስመ ጋኔን በሀም
አኀዞ ።
፲፰ ወኀበ ረከቦ ይነጽሖ ወያስተራግፆ ወያሴውኖ ወያሐ
ቅዮ ስነኒሁ ወያየብሶ ወእቤሎሙ ለአርዳኢከ ያው
ፅዕዎ ወስእንዎ ፈውሶቶ ።

፲፱ ወአውሥአ ወይቤሎሙ አ ትውልድ እንተ አልባቲ
ሃይማኖት እስከ ማእዜኑ እሄሉ ምስሌክሙ ወእስከ
ማእዜኑ እትዔገሠክሙ አምጽእዎ ዝየ ኀቤየ ።

፳ ወወሰድዎ ኀቤሁ ወሶበ ርእዮ ውእቱ ጋኔን ነፅሖ
ሶቤሃ ውስተ ምድር ወአስተራገፆ ወአስወኖ ።



ጴጥሮስም መልሶ ጌታ ኢየሱስን መምህር ሆይ! ፭
ከዚህ ብንቀመጥ ይሻለናል ሦስት ዳስ እንሥራ፡ አን
ዱን ላንተ፡ አንዱን ለሙሴ፡ አንዱን ለኤልያስ፡ አለው።
ደንግጠው ነበርና የሚናገረውን አያውቅም ነበር ። ፮
ብሩህ ደመና መጥቶ ከበባቸው "የምወደው ልጄ ፯
ይህ ነው፡ እርሱን ስሙት የሚል ቃል ከደመና
መጣ" ። ፪ ጴጥ ፩ ፡ ፲፯ - ፲፰ ።
ከዚህም በኋላ ድንገት ቀና ብለው በተመለከቱ ጊዜ ፰
ጌታ ኢየሱስ ብቻውን ከነርሱ ጋር ከመኖሩ በቀር
ያዩት የለም ።
ከተራራውም ሲወርዱ ጌታ ኢየሱስ ያዩትን ለማ ፱
ንም ለማን እንዳይናገሩ አዘዛቸው የሰው ልጅ ከሙ
ታን ተለይቶ በሚነሣበት ጊዜ ካልሆነ በቀር ። ምዕ
፲፰ ፡ ፴፩ ።
ቃሉንም ተቀበሉ፡ ከሙታን ተለይቶ መነሣት ምን ፲
ድር ነው? እያሉ እርስ በርሳቸው ተመራመሩ ።
ደቀ መዛሙርቱም ጻፎችና ፈሪሳውያን ለምን ኤል ፲፩
ያስ አስቀድሞ ይመጣል ይላሉ? ብለው ጠየቁት ።
እሱም መልሶ እንዲህ አላቸው ኤልያስ አስቀድሞ ፲፪
ይመጣል፡ ሁሉንም ያቀናናል፡ እንኪያ ብዙ መከራ
እንደሚያጸኑበትና እንደሚንቁት ስለ ሰው ልጅ
ስለምን ተጻፈ? ኢሳ ፶፫ ፡ ፫ ።
ነገር ግን እላችኋለሁ ኤልያስ በእርግጥ መጣ ስለ ፲፫
እርሱ እንደ ተጻፈው የወደዱትን ሁሉ አደረጉበት ።
ማቴ ፲፩ ፡ ፲፬ ። ፩ ነገ ፲፱ ፡ ፪ - ፲ ።
ወደ ደቀ መዛሙርቱም በመጣ ጊዜ ብዙ ሰዎች ከነ ፲፬
ርሱ ተሰብስበው ጻፎችም ሲጠይቋቸው አገኘ ።
ማቴ ፲፯ ፡ ፲፬ - ፳፩ ። ሉቃ ፱ ፡ ፴፯ - ፵፪ ።
ሰዎችም ሁሉ ባዩት ጊዜ ደንግጠው ሮጡና እጅ ፲፭
ነሡት ።
ጻፎችንም ለምን ትከራከሯቸዋላችሁ? ብሎ ጠየ ፲፮
ቃቸው ።

## ክፍል ፵፡ ጋኔን ይጥለው ስለ ነበረ ሰው ።

ከሕዝቡ መካከልም አንድ ሰው መልሶ እንዲህ አለ፡ ፲፯
መምህር! ልጄን ወዳንተ አምጥቸዋለሁ ድዳ ጋኔን
ይዞታልና ።
ባገኘበትም በታ ላይ ይጥለዋል፡ ያራግጠዋል፡ አረፋ ፲፰
ያስደፍቀዋል (ያሽናዋል) ጥርሱን ያፋጩዋል፡ ያደር
ቀዋል፡ ያወጡትም ዘንድ ለደቀ መዛሙርትህ ነገር
ኳቸው ግን መፈወስ ተሳናቸው ።
እርሱም መልሶ ሃይማኖት የሌላት ትውልድ ሆይ! ፲፱
እስከ መቼ ድረስ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ፡ እስከ
መቼስ እታገሣችኋለሁ፡ ወደዚህ ወደኔ አምጡት
አላቸው ።
ወደርሱም ወሰዱት፡ ያም ጋኔን ባየው ጊዜ ወድ ፳
ያው በመሬት ላይ ጣለው አንፈራገጠው አረፋ
አስደፈቀው ።

## ወንጌል ዘማርቆስ ፲ ።

፮ ወእምፍጥረትሰ ተባዕተ ወአንስተ ገብረ እግዚአ
ብሔር ።
፯ ወበእንተ ዝንቱ የኃድግ ብእሲ አባሁ ወእሞ ወይተ
ልዋ ለብእሲቱ ።
፰ ወይከውኑ ክልኤሆሙ አሐደ ሥጋ ናሁኬ ኢኮኑ
ክልኤተ አላ አሐዱ ሥጋ እሙንቱ ።
፱ ዘእግዚአብሔር እንከ አስተፃመረ ሰብእ ኢይፍልጥ ።
፲ ወበቤት ካዕበ ተስእልዎ አርዳኢሁ በእንተ ዝንቱ ።
፲፩ ወይቤሎሙ ዘደኃረ ብእሲቶ ወሐረ ካልእተ ፥ ዘመወ
ላዕሌሃ ።
፲፪ ወእንተሂ ደኃራ ምታ ወሐረት ካልአ ፥ ዘመወት ።

### ክፍል ፵ወ፩ ፥ በእንተ ባርኮቱ ሕፃናተ ።

፲፫ ወአምጽኡ ኀቤሁ ሕፃናተ ይግሥሦሙ ወገሠፅዎሙ
አርዳኢሁ ለእለ አቅረብዎሙ ።
፲፬ ወርእዮ እግዚእ ኢየሱስ ተምዐ ወይቤሎሙ ኅድጉ
ሕፃናተ ይምጽኡ ኀቤየ ወኢትክልእዎሙ ፥ እስመ
ለዘከመ እሉ ይእቲ መንግሥተ እግዚአብሔር ።
፲፭ አማን እብለክሙ ዘኢተቀበላ ለመንግሥተ እግዚአ
ብሔር ከመ ሕፃናት ኢይበውኣ ።
፲፮ ወአንበሮሙ ውስተ ሕፅኑ ወባረኮሙ ወወደየ እዴሁ
ዲቤሆሙ ።

### ክፍል ፵ወ፪ ፥ በእንተ ወሬዛ ባዕል ።

፲፯ ወእንዘ የሐውር በፍኖት መጽአ አሐዱ ብእሲ ወሰ
ገደ ሎቱ ወይቤሎ ሊቅ ኄር ምንተ እግበር ከመ
እረስ ሕይወተ ዘለዓለም ።
፲፰ ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ምንተ ትብለኒ ኄር አልቦ
ኄር ዘእንበለ አሐዱ እግዚአብሔር ።
፲፱ ተአምር ትእዛዛተ ኢትሐር ብእሲተ ብእሲ ፥ ኢትቅ
ትል ነፍሰ ፥ ኢትስርቅ ፥ ኢትኩን ስምዐ በሐሰት ፥
ወኢትሂድ ፥ ወአክብር አባከ ወእመከ ።
፳ ወአውሥአ ወይቤሎ ሊቅ ዘንተሰ ኵሎ ዐቀብኩ
እምንእስየ ።
፳፩ ወነጸሮ እግዚእ ኢየሱስ ወአፍቀሮ ወይቤሎ አመሰ
ትፈቅድ ፍጹመ ትኩን አሐቲ ተርፈተከ ሑር ሢጥ
ኵሎ ዘብከ ወሀብ ለነዳያን ወትረክብ መዝገበ በሰ
ማያት ወፁር መስቀለ ሞትከ ወነዓ ትልወኒ ።
፳፪ ወተከዘ በእንተ ዝንቱ ነገር ወሐረ ትኩዞ እስመ
ብዙኀ ጥሪቱ ።
፳፫ ወነጸሮሙ እግዚእ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ ወይቤሎሙ
እፎ ዕፁብ ለዘቦ ንዋይ በዊአ ውስተ መንግሥተ
ሰማያት ።

## የማርቆስ ወንጌል ፲ ።

ከፍጥረት መጀመርያ ግን እግዚአብሔር ወንድና ፮
ሴትን ፈጠረ ። ዘፍ ፩ ፡ ፳፯ ።
ስለዚህም ወንድ ፥ አባቱንና እናቱን ትቶ ሚስቱን ፯
ይከተላል ። ዘፍ ፪ ፡ ፳፬ ።
ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ ፥ እንግዲህ አንድ ፰
አካል ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም ።
እንግዲህ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ፱
አይለይ ።
ዳግመኛም በቤት ፥ ደቀ መዛሙርቱ ስለዚሁ ነገር ፲
ጠየቁት ።
ሚስቱን የፈታ ወደ ሌላዪቱም የሄደ ፥ በእሷ አመነ ፲፩
ዘረ አላቸው ።
ባሏ የፈታትና ወደ ሌላ ወንድ የሄደችም፥አመነዘረች። ፲፪

### ክፍል ፵፩ ፥ ሕፃናትን ስለ መባረኩ ።

ይዳሥሣቸው ዘንድ ሕፃናትን ወደርሱ አመጡ ፥ ደቀ ፲፫
መዛሙርቱ ግን ያመጧቸውን ተቈጧቸው ። ማቴ
፲፱ ፥ ፲፫ - ፲፭ ። ሉቃ ፲፰ ፥ ፲፭ - ፲፯ ።
ጌታ ኢየሱስም አይቶ ተቈጣና እንዲህ አላቸው ፲፬
ሕፃናትን ተዉ ወደ እኔ ይምጡ አትከልክሏቸው ፥
መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና ።
እውነት እነግራችኋለሁ የእግዚአብሔርን መንግ ፲፭
ሥት እንደ ሕፃናት ያልተቀበላት አይገባበትም ።
ማቴ ፲፰ ፥ ፫ - ፮ ።
በእጠገቡም አስቀምጦ እጁን ጭኖ ባረካቸው ። ምዕ ፲፮
፱ ፥ ፴፮ ።

### ክፍል ፵፪ ፥ ስለ ጐልማሳው ባለጠጋ ።

በመንገድ ሲሄድ አንድ ሰው መጥቶ ሰገደለትና ቸር ፲፯
መምህር! የዘለዓለም ሕይወትን እወርስ ዘንድ ምን
ላድርግ? አለው ።
ጌታ ኢየሱስም እንዲህ አለው ፥ ምን ቸር ትለኛለህ ፲፰
ከአንድ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር የለም ።
ትእዛዛትን ታውቃለህ ወደ ጐልማሳ ሚስት አትሂድ ፥ ፲፱
ነፍስ አትግደል ፥ አትስረቅ ፥ በሐሰት አትመስክር ፥
አትቀማ ፥ አባትህንና እናትህን አክብር ። ዘፀ ፳ ፥ ፲፪።
እርሱም መልሶ መምህር! ይህንስ ሁሉ ከሕፃንነቴ ፳
ጀምሬ ጠብቄአለሁ አለው ።
ጌታ ኢየሱስም አይቶ ወደደውና ፍጹም ልትሆን ፳፩
ብትወድስ አንዲት ነገር ቀርታሃለች ፥ ሂድና ያለህን
ሁሉ ሸጠህ ለነዳያን ስጥ በሰማያትም መዝገብን ታገ
ኛለህ ፥ የመከራህንም መስቀል ተሸክምና ተከተለኝ
አለው ። ማቴ ፲ ፥ ፴፰ ።
ስለዚህም ነገር አዘነ ፥ አዝኖም ሄደ ገንዘቡ ብዙ ፳፪
ነበርና ።
ጌታ ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን አየት አደረገና ፳፫
ገንዘብ ላለው ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት
መግባት እንዴት ጭንቅ ነው አላቸው ።

፪ ወተስእሎ ጲላጦስ ወይቤሎ አንተኑ ንጉሦሙ ለአይ
ሁድ ፡ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎ አንተ
ትብል ።
፫ ወአስተዋደይዎ ሊቃነ ካህናት ብዙኃ ፡ ወውእቱሰ
አልቦ ዘአውሥአ ።
፬ ወሐተቶ ካዕበ ጲላጦስ ወይቤሎ አልቦኑ ዘትሰጠው
እንዘ መጠነዝ ያስተዋድዩከ ።
፭ ወኢተሰጥዎ እግዚእ ኢየሱስ ወኢምንተኒ ፡ እስከ
አንከሮ ጲላጦስ ።
፮ ወለለበዓል ያሐዩ ሎሙ አሐደ እምነ ሙቁሐን ዘአ
ብደሩ ።
፯ ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ዘስሙ በርባን ሙቁሕ ምስለ
እለ ገብሩ ሀከከ ወምስለ ቀተልተ ነፍስ ።
፰ ወዐርጉ ሕዝብ ወከልሑ ወሰአሉ ይግበር ሎሙ
በከመ ያለምዶ ።
፱ ወአውሥአ ጲላጦስ ወይቤሎሙ ትፈቅዱኑ አሕይዎ
ለክሙ ለንጉሠ አይሁድ ።
፲ እስመ የአምር ከመ በቅንአቶሙ አግብእዎ ሊቃነ
ካህናት ።
፲፩ ወሊቃነ ካህናትሰ ሆከምዎሙ ለሕዝብ ከመ በርባንሃ
ይስአሉ ያሕዩ ሎሙ ።
፲፪ ወካዕበ አውሥአ ጲላጦስ ወይቤሎሙ ምንተ እንከ
ትፈቅዱ እረስዮ ለዘተብሀለ ንጉሠ አይሁድ ።

፲፫ ወካዕበ ከልሑ ኵሎሙ ወይቤሉ ስቅሎ ።
፲፬ ወይቤሎሙ ጲላጦስ ምንተ እኩየ ገብረ ፡ ወፈድፋደ
ጸርሑ ወይቤሉ ስቅሎ ።
፲፭ ወመከረ ጲላጦስ ይግበር ፈቃዶሙ ለሕዝብ ወአሕ
የወ ሎሙ በርባንሃ ወቀሠፎ ለእግዚእ ኢየሱስ ፡
ወወሀቦሙ ይስቅልዎ ።

## ክፍል ፸ወ፮ ፡ በእንተ ተሣልቆቶሙ ላዕለ እግዚእነ ።

፲፮ ወአብእዎ ሐራ ውሣጤ ዐፀድ ኀበ ምኵናን ወጸ
ውዑ ኵሎ ሠገራተ ሰጺራ ።
፲፯ ወአልበስዎ ሜላተ ወፀፈሩ አክሊለ ዘሦክ ወአስተ
ቀጸልዎ ላዕለ ርእሱ ወተሣለቅዎ ።
፲፰ ወይብልዎ በሐ ንጉሦሙ ለአይሁድ ።
፲፱ ወይኰርዕዎ ርእሶ በሕለት ፡ ወይዌርቅዎ ፡ ወያስተበ
ርኩ ወይሰግዱ ሎቱ ።
፳ ወሰበ ተሣለቁ ላዕሌሁ ሰለብዎ ውእተ ሜላተ ፡ ወአ
ልበስዎ አልባሲሁ ወወሰድዎ ኀበ ይሰቅልዎ ።
፳፩ ወዐበጡ አሐደ እምኀለፍት ስምዖንሃ ቀሬናዌ እት
ወቶ እምሐቅል ወውእቱ አቡሆሙ ለእለ እስክን
ድሮስ ወለሩፎስ ከመ ይፁር መስቀሎ ።

፳፪ ወወሰድዎ ብሔረ ጎልጎታ ዘበትርጓሜሁ ይብልዎ
መካነ ቀራንዮ ።



ጲላጦስም የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን ? ብሎ ጠየ ፪
ቀው ፡ ጌታ ኢየሱስም መልሶ አንተ ትላለህ አለው ።

የካህናት አለቆችም ብዙ አሳጡት ፡ እሱ ግን የመለ ፫
ሰው ነገር የለም ።
ጲላጦስም ይህን ያህል ሲያሳጡህ አትመልስምን ? ፬
ብሎ እንደገና ጠየቀው ።
ጌታ ኢየሱስም ጲላጦስ እስኪያደንቀው ድረስ ምንም ፭
ምን አልመለሰለትም ። ምዕ ፲፬ ፡ ፷፬ ። ኢሳ ፶፫ ፡ ፯ ።
በበዓል በበዓልም ከእሥረኞች የመረጡትን አንዱን ፮
ይፈታላቸው ነበር ።
ከነፍስ ገዳዮችና ከክፉ አድራጊዎች ጋር የታሠረ ፯
ስሙ በርባን የሚባል አንድ ሰው ነበር ።
ሕዝቡም እንደ ልማዱ ያደርግላቸው ዘንድ እየ ፰
ጮኹ ለመኑ ።
ጲላጦስም መልሶ የአይሁድን ንጉሥ ላድንላችሁ ፱
ትወዳላችሁ ? አላቸው ።
የካህናት አለቆች ቀንተው አሳልፈው እንደ ሰጡት ፲
ያውቃልና ። ዮሐ ፲፩ ፡ ፵፰ ።
የካህናት አለቆች ግን በርባንን እንዲያድንላቸው ፲፩
ይለምኑት ዘንድ ሕዝቡን አነሣሡዋቸው ።
ጲላጦስም እንደገና መልሶ እንግዲህ የአይሁድ ፲፪
ንጉሥ የተባለውን ምን ላደርገው ትወዳላችሁ ?
አላቸው ።
ሁሉም እንደገና ስቀለው እያሉ ጮኹ ። ፲፫
ጲላጦስም ምን ክፉ ሥራ ሠራ ? አላቸው ፡ እነሱ ፲፬
ግን ስቀለው እያሉ በጣም ጮኹ ።
ጲላጣስም የሕዝቡን ፈቃድ ላድርግ አለና በርባንን ፲፭
ፈታላቸው ፡ ጌታ ኢየሱስን ግን ገርፎ ሊሰቅሉት
ሰጣቸው ።

## ክፍል ፸፮ ፡ በጌታችን ላይ ስለ መዘባበታቸው ።

ወታደሮችም ወደ ግቢ ውስጥ ወደ ፍርድ መቀበ ፲፮
ያው አገቡት ፡ ባለወንቹን ጭፍሮች ሁሉ ጠሩ ።
ነጭ ሐርን አለበሱት የእሾህ አክሊል ታትተው ፲፯
በራሱ ላይ ደፉበትና ተዘባበቱበት ።
የአይሁድ ንጉሥ ሰላምታ ይገባሃል ይሉት ነበር ። ፲፰
ራሱን በዘንግ ይመቱት ፡ ይተፉበት ፡ ተንበርክከውም ፲፱
ይሰግዱለት ነበር ።
በተዘባበቱበትም ጊዜ ያንን ነጩን ሐር ገፈፉና ፡ ፳
ልብሱን አልብሰው ወደሚሰቅሉበት ቦታ ወሰዱት ።
መስቀሉንም ይሸከም ዘንድ የቀሬን ሰው የሆነ አንድ ፳፩
ስምዖን የሚባል መንገድ አላፊ ከበረኻ ሲመለስ
ያዙ ፡ እሱም የእለ እስክንድሮስና የሮፎስ አባት
ነው ። ሮሜ ፲፮ ፡ ፲፫ ።
ትርጓሜው የራስ ቅል ወደሚሉት ወደ ጎልጎታ ፳፪
ሥፍራ ወሰዱት ።

